# የኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ ክፍያ (EIP): የማነቃቂያ ቼክ

CASH CAMPAIGN OF MARYLAND
Creating Assets, Savings and Hope

## ምንድን ነው?

የኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ ክፍያ (EIP) የማነቃቂያ ቼክ እየተባለም ይጠራል። ይህ በመንግስት የሚከፈል የአንድ ጊዜ ክፍያ ሲሆን በ COVID-19 ምክንያት የተከሰተ የኑሮ ጫናን ለማቃለል የሚሰጥ ነው።

| ለግለሰብ | በጋራ |
|---|---|
| $1, 200 | $2,400 |
| ✷ ዕድሜው ከ17 ዓመት በታች ለሆነ እያንዳንዱ ልጅ $500 ይሰጣል | |

## እርስዎ ብቁ ነዎት?

የአሜሪካ ዜጋ፣ ቋሚ ነዋሪ ወይም የሚከተሉትን መስፈርቶች ያሟሉ የውጭ ሃገር ዜጋ ከሆኑ ብቁ ነዎት:

- ✓ የጸና የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር ካለዎት
- ✓ የሌላ ግብር ከፋይ ጥገኛ አለመሆንዎት ከተረጋገጠ
- ✓ የተስተካከለ አጠቃላይ ገቢዎ በተወሰነ መጠን ስር የሚወድቅ ከሆነ

## የማመለከተው እንዴት ነው? ግብርዎን ያሳውቁ

አንዳንድ ሰዎች ክፍያቸውን ወዲያውኑ ያገኛሉ:

- ለ2018 ወይም 2019 የፌዴራል ገቢ ግብራቸውን ያሳወቁ ግለሰቦች

እንዲሁም፣ የሚከተሉትን ክፍያዎች የሚያገኙ ሰዎች:

- የማህበራዊ ዋስትና ጡረታ
- የአካል ጉዳተኝነት ጥቅማ ጥቅም (SSDI)
- የጥቃት ሰለባዎች ጥቅማ ጥቅሞች
- ተጨማሪ የማህበራዊ ዋስትና ገቢ (SSI) ተቀባዮች
- የቀድሞ ጦር አባላት ጉዳዮች ጥቅማ ጥቅም ካሳ እና
- የጡረታ (C&P) ጥቅማ ጥቅም ተቀባዮች
- የባቡር መንገድ የጡረታ (RRB) ጥቅማ ጥቅሞች

## ግብር የማሳያውቁ ሰዎች

✷ ገቢያቸው ዝቅተኛ የሆነ ወይም ምንም ገቢ የሌላቸውና የግብር ተመላሽ ያላቀረቡ ሰዎች ክፍያውን ለማግኘት ብቁ ናቸው። ወደ IRSwebsite በመግባት ግብር የማያሳውቅ ሰው ቅጽ መሙላት አለባቸው።

ግብር የማያሳውቅ ሰው ቅጽ ላይ የሚያስፈልግ መረጃ:

- ሙሉ ስም፣ ወቅታዊ የመልእክት መቀበያ አድራሻና የኢሜይል አድራሻ
- የትልውልደ ቀንና የጸና የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር
- የባንክ ሒሳብ ቁጥር፣ የሒሳቡ ዓይነትና ራውቲንግ ቁጥር (ካለ)
- በዚህ ዓመት መጀመሪያ ላይ ከ IRS የተሰጠዎት ማንነትን መጠበቂያ የግል መታወቂያ ቁጥር (IP PIN) ካለ
- የመንጃ ፈቃድ ወይም በግዛት የተሰጠ መታወቂያ ካርድ ካለዎት
- በ2019 መስፈርቱን ለሚያሟላ ለእያንዳንዱ ልጅ: ስም፣ የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር ወይም የጉዲፈቻ የግብር ከፋያ መለያ ቁጥር እና ከእርስዎ ወይም ከባለቤትዎ ጋር ያለው ዝምድና

## ቀነ ገደቦች

### ግብር ማሳወቂያ

ጁላይ 15

✷ግብርዎን እስከ ጁላይ 15 ድረስ ለማሳወቅ ካልቻሉ የጊዜ ማራዘሚያ ለማግኘት ማመልከት አለብዎ።

✷ጁላይ 15 ለ IRS የሚገባ ግብር የሚከፈልበት የመጨረሻ ቀን ነው።

✷ከጁላይ 15 በኋላ፣ ለ IRS መከፈል የሚገባው ክፍያ ቅጣት እየወለደ ይሄዳል።

### የማራዘሚያ ቀን

ኦክቶበር 15

✷ ይህ ግብር ለማሳወቅ የሚፈቀድ የጊዜ ማራዘሚያ ነው።

✷ይህ ለ IRS መከፈል ያለበትን ግብር ለመክፈል የሚሰጥ የጊዜ ማራዘሚያ **አይደለም** ።

✷ይህ የማነቃቂያ ቼክ ለማግኘት መረጃዎን የሚያቀርቡበት የመጨረሻ ቀን ነው።

# የክፍያ መረጃ

✷ ክፍያዎትን ማግኘት የሚችሉባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ።

| | |
|---|---|
| ቀጥተኛ ተቀማጭ | ቀጥተኛ ተቀማጭ ገንዘብዎን በፍጥነት ለማግኘት የሚችሉበት ዘዴ ነው። ክፍያው እርስዎ በግብር ተመላሽ ወይም ግብር በማያሳውቅ ሰው ቅጽ ላይ ወደሞሉት የባንክ ሒሳብዎ ገቢ ይደረጋል። |
| በፖስታ | የባንክ ሒሳብ መረጃዎን ካላሳወቁ፣ ክፍያዎ በፖስታ ቤት በኩል ይላክልዎታል።<br><br>ክፍያው በቼክ ወይም በቅድመ ክፍያ ዴቢት ካርድ ወጪ ይደረጋል። |

## የቅድመ ክፍያ ዴቢት ካርድ

✷ የቅድመ ክፍያ ዴቢት ካርድ ተመላሽ አድራሻ ባለው ኤንቨሎፕ የሚላክ ሲሆን፣ ላኪውም ***Money Network Cardholder Services***ነው።

✷ ቪዛ ካርድ በሚቀበሉ ቦታዎች ሁሉ የቅድመ ክፍያ ካርድዎን መጠቀም ይችላሉ።

✷ የቅድመ ክፍያ ካርድዎን በመጠቀም ጥሬ ገንዘብ ማግኘት ይችላሉ። እባክዎ የክፍያዎችን ዝርዝር ለማየት eipcard.com ይጎብኙ።

✷ ካርድዎን ስራ ለማስጀመር ወደ 1.800.240.8100 መደወል አለብዎት።

✷ <u>ካርዱን ስራ ለማስጀመር የሚያስፈልግ መረጃ፡</u>

- የካርድ ቁጥር
- የማህበራዊ ዋስትና ቁጥርዎ የመጨረሻዎቹ 6 ዲጂቶች
- ከካርድዎ በስተጀርባ ላይ የተጻፈ ባለ 3 ዲጂት የሴኪዩሪቲ ኮድ

**ለተጨማሪ መረጃ፣ ይህን ይጎብኙ፡ irs.gov**